የአላህ ፊት የሚፈለግበትን እውቀት የዱንያን ጥቅም ለማግኘት ካልሆነ በቀር ለሌላ ግብ የማይማረው ከሆነ የትንሳኤ ቀን የጀነትን ሽታ አያገኝም።

ከአቡ ሁረይራ ረዲየላሁ ዐንሁ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፦ «የአላህ መልዕክተኛ -
የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- እንዲህ ብለዋል፡ "የአላህ ፊት የሚፈለግበትን እውቀት የዱንያን ጥቅም ለማግኘት ካልሆነ በቀር ለሌላ ግብ የማይማረው ከሆነ የትንሳኤ ቀን የጀነትን ሽታ አያገኝም።"» [ሶሒሕ ነው።] [አቡዳውድ፣ ኢብኑ ማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

ነቢዩ -የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- በመሰረቱ የአላህ ውዴታ የሚፈለግበትን ሸሪዓዊ እውቀትን የተማረ ሰው ሲማረው ግን ገንዘብን ወይም ክብርን የመሰሉ የዱንያ መጣቀሚያና ዕጣፈንታዎችን ለማግኘት ካልሆነ በቀር የማይማረው የሆነ ሰው የትንሳኤ ቀን የጀነትን ሽታ አያገኝም አሉ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/6262